Hans-Jörg Ronsdorf

መስቀሉ ከእኛ ጋር
ምን ግንኙነት አለው

ቀላል።
ግልጽ።



ኢየሱስ ለምን መሞት ነበረበት?

ኢየሱስ ለምን መሞት ነበረበት?

መሰቀሉ ከእኛ ጋር ምን ግንኙነት አለው

Hans-Jörg Ronsdorf

1ኛ እትም (የጀርመንኛው እትም)፣ ኦክቶበር 2026 (እ.ኤ.አ.)፣ Sulzberg
መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
የሽፋን ንድፍ፦ Christine Ronsdorf
የመጽሐፍ ቅዱስ ቃላት በነጻ ተተርጉመዋል
ለማዘዝ፣ ለጥያቄና ለግንኙነት፦ hj-ronsdorf@t-online.de

እግዚአብሔር ግን ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ **ስለ እኛ** በመሞቱ ፍቅሩን ለእኛ ያሳያል።

ሮሜ 5፥8

ይህ ትንሽ መጽሐፍ አንድ ጥያቄ ብቻ ይመረምራል፦ ከሁለት ሺህ ዓመት በፊት የአንድ ሰው ሞት ዛሬ እኔን ለምን ይረዳኛል? የተጻፈው ከቤተ ክርስቲያን ጋር ብዙም ግንኙነት ለሌላቸው አንባቢዎች ነው። ደረጃ በደረጃ፣ በቀላል ቃላት።

ማውጫ

1 አንድ ቀላል ጥያቄ 6
2 በእኛ ላይ ያለው ችግር 8
3 እግዚአብሔር በእውነት ምን ዓይነት ነው 11
4 ለምን ደም? 13
5 ኢየሱስ ራሱ የተናገረው 15
6 ሦስት ከባድ ዓረፍተ ነገሮች 17
7 ሞቱ እንዴት ያድነናል 20
8 ትንሣኤ ለምን የታሪኩ አካል ነው 23
9 የምሥራቹ 25

1 አንድ ቀላል ጥያቄ

ከሁለት ሺህ ዓመት በፊት አንድ ሰው በሞት ፍርድ ተገደለ። ከከተማው ውጭ፣ ከከተማው ቅጥር ፊት ለፊት። በእንጨት ግንድ ላይ፣ በእንጨት መሰቀል ላይ። ዓመፅን በለመዱ ጉጉ ተመልካቾች ፊት። በዚያን ጊዜ ብዙዎች እንዲህ ሞቱ። ሮማውያን በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎችን ገደሉ፤ ብዙዎችን ሰቀሉ። ትርጉም የሌላቸው ሞቶች።

ክርስቲያኖች ስለዚህ ስለ አንዱ ሰው እሰከ ዛሬ አንድ እንግዳ ዓረፍተ ነገር ይናገራሉ። ስለ እኛ ሞተ ይላሉ። «ስለ እኛ» ምን ማለት ነው? የዚህ የአንዱ ሞት ልዩነቱ ምንድር ነው?

ለሌሎች ሲሉ የሞቱ ሰዎች ነበሩ፤ ዛሬም አሉ። ሌሎችን ከሞት ማዳን የሚችሉት በዚህ መንገድ ብቻ ሲሆን። ራስን ለሌሎች አሳልፎ ከመስጠት የሚበልጥ ነገር ማድረግ አይቻልም። እነርሱ በሕይወት እንዲኖሩ።

ቀደም ሲል፣ ክትባት ከመኖሩ በፊት፣ ልጆች በዲፍቴሪያ ታፍነው ይሞቱ ነበር። የሚያጣብቅ ሽፋን ጉሮሮአቸውን ይዘጋ ነበር። አንዳንድ ጊዜ የሚረዳው አንድ ነገር ብቻ ነበር። ሐኪሙ ትንሽ ቱቦ አስገብቶ ሽፋኑን በራሱ አፍ ይመጠው ነበር። ልጁ እንደገና መተንፈስ ቻለ። ሐኪሙ ግን አሁን በሽታውን በውስጡ ያዘ። አንዳንዶቹ በዚህ ሞተዋል።

ሐኪሙ የረዳው ብቻ አይደለም። ልጁን ይገድል የነበረውን ወደ ራሱ ወሰደ። በሽታው ከልጁ ወጥቶ ወደ ሐኪሙ ገባ።

ጥያቄው የሚጀምረው በትክክል እዚህ ነው። ኢየሱስ ስለ እኛ ከሞተ፦ ታዲያ ከምን አዳነን? ይህን ምሳሌ ወደ እኛ ብናመጣው በሽታው ምን ነበር? የትስ ነበር?

አብዛኞቹ ሰዎች ምንም በሽታ አይሰማቸውም። ይኖራሉ፣ ይሠራሉ፣ ይወዳሉ፣ የሚችሉትን ሁሉ ያደርጋሉ። በሽታ? የት? በሽታ ቢኖርስ እንኳ ከሁለት ሺህ ዓመት በፊት የአንድ ሰው ሞት ለምን ይፈውሰዋል? አንድ ሰው በኢየሩሳሌም ሞተ። እኔ የምኖረው እዚህ ነው።

መሰቀሉ ከእኔ ጋር ምን ግንኙነት አለው? ይህ የየዋህ ጥያቄ አይደለም። ለክርስትና ሊቀርብ የሚችል ከሁሉ የሚበልጠው ጥያቄ ነው። በዚህ ትንሽ መጽሐፍ ውስጥ ይህንን አንድ ጥያቄ ለመመለስ ከመሞከር በቀር ሌላ ምንም ማድረግ አልፈልግም። ደረጃ በደረጃ። በመጀመሪያ፦ የምንሠቃየው በምንድር ነው? ከዚያ፦ ይህን ከእኛ የሚወስደው ማን ነው? ከዚያ፦ በእርሱ ላይ ምን ይሆናል? በመጨረሻም፦ ይህ ወደ እኔ እንዴት ይደርሳል?

ከመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች አንዱ ይህን ዓረፍተ ነገር በበለጠ ግልጽነት ተናግሮታል። ኢየሱስ በደላችንን በገዛ አካሉ፣ እዚያ በእንጨቱ ላይ – በመስቀሉ ላይ – ተሸከመ ብሎ ጻፈ። በቁስሉም እኛ ተፈወስን።[1]

ከዚህ ዓረፍተ ነገር ሦስት ቃላትን ያስታውሱ፦

ተሸከመ። እካል። ፈውስ።

በእነዚህ ላይ ጥቂት እንቆያለን።

1. 1 ጴጥሮስ 2፥24

2 በእኛ ላይ ያለው ችግር

በእግዚአብሔር አልጀምርም።

ጉዳዩ ስለ እኛ ነው።

ማን እንደ ወለደንና የት እንደ ተወለድን ከእኛ ማንም መምረጥ አልቻለም። ሕይወት ወደ የትኛው ሁኔታ እንደ ጣለን የእኛ ውሳኔ አልነበረም። ዛሬ ያለንበትንም ቦታ ብዙ ጊዜ የወሰንነው እኛ አይደለንም።

አሁን ጉዳዩ በምዕራፍ 1 እንዳለው ልጅ የአካል በሽታ አይደለም። ጉዳዩ የማይጨበጥ በሽታና እንዴት እንደሚሰማን ነው፦ ባዶነት፣ ትርጉም አልባነት፣ የበደለኝነት ስሜት፣ መሰበር፣ መውጫ ማጣት፣ መታሰር፣ ተስፋ ማጣት። ይህንን ሁሉ ማንም ሊሰማው አይፈልግም። በቅንነት ቆም ብሎ የሚያሰብ ሰው እንደነዚህ ያሉትንና ተመሳሳይ ስሜቶችን ሊያስተውል ይችላል።

ብዙ ጊዜ የሚመጡት ጸጥ ባለ ቅጽበት ነው። ሌሊት እነቅልፍ ሲያጡ። በመቃብር አጠገብ። ወይም አንድ ሰው ከእርሰዎ ጋር መነጋገር ሲያቆም። ያኔ ገፍተው ሊያስወግዱት የማይችሉት አንድ ነገር አለ።

እያንዳንዱ ሰው ከእንግዲህ ሊያስተካክለው የማይችል ነገር አለው። ከአፍ የወጣ ቃል። በኃይል የተዘጋ በር። ከመታረቅዎ በፊት የሞተ ሰው። ማንም ያላስተዋለው፣ እርስዎ ግን ራስዎ ፈጽሞ የማይረሱት ማጭበርበር።

ብዙ ነገር ማድረግ ይችላሉ። ጥፋትዎን ሊገነዘቡ ይችላሉ። ይቅርታ ሊጠይቁ ይችላሉ። በተቻለ መጠን ጉዳቱን ሊክሱ ይችላሉ። ዳግመኛ ላለማድረግ ሊወስኑ ይችላሉ።

ግንዛቤው የሚመጣው ዘግይቶ ነው። ይቅርታው ሌላውን ሰው ከእንግዲህ አያገኘውም። ጉዳቱ ሊካስ አይችልም፤ ምክንያቱም ለእርሱ የሚሆን ገንዘብ የለም። ወይም ፈጽሞ የማይቻል ስለ ሆነ። ውሳኔውም የሚጸናው እሰከሚቀጥለው ጊዜ ብቻ ነው።

ሁሉም ቢሳካ እንኳ አንድ ነገር ይቀራል። ነገሩ ተፈጽሟል። በዓለም ውስጥ አለ። ምንም ካሳ እንዳልተፈጸመ ሊያደርገው አይችልም።

እስካሁን የተመለከትነው እኛን ሰዎችን ብቻ ነው። እግዚአብሔር ፈጣሪያችን ቢሆንስ? ዓለምን የፈጠርነው እኛ አይደለንም። የተፈጥሮ ሕጎችንም አይደለም። በደልን እንዴት እንደምንይዘው ወይም በእውነት እንዴት እንደምንገላገለው የሚወስኑትን ሕጎችና

ሁኔታዎችም አይደለም። የተወለድንባት ዓለም የእግዚአብሔር ዓለም ናት። ሌላ ቢመሰለንም፦ ሕጎቹን የምንወሰነው እኛ አይደለንም።

ከላይ የጠቀስኩትን ሁሉ ከገዳይ በሽታ ጋር ልናነጻጽረው እንችላለን። መጽሐፍ ቅዱስ ለዚህ አጭር ቃል አለው፦ ኃጢአት።

«ኃጢአት» የሚለው ቃል አርጅቷል። ብዙዎች በውሰጡ የሚሰሙት የሥነ ምግባር ሰብከትንና የተነሣ የማሰጠንቀቂያ ጣትን ብቻ ነው። የታሰበው ግን ከሕይወት ጋር በጣም የተቆራኘ ነገር ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የሚጠቀምበት ቃል ቃል በቃል «ዒላማን መሳት» ማለት ነው። ዒላማውን እንደሚሰት ፍላጻ።

ስለዚህ ኃጢአት ማለት፦ መሆን የሚገባኝ ሰው እይደለሁም ማለት ነው። መደረግ የሌለበትንም አድርጌአለሁ። ሁለቱም አብረው ይሄዳሉ። ድርጊቶቹን ያመለክታል። እነርሱ ሊቆጠሩ ይችላሉ። እነዚህ ድርጊቶች የሚመነጩበትን የማንነታችንን አንድ ክፍልም ያመለክታል። እርሱ ሊቆጠር አይችልም። ግን ሁሉም ያውቀዋል። አንድ ነገር ለማድረግ ያሰባሉ፤ ከዚያም ሌላውን ያደርጋሉ። እንደሚገፋን ኃይል። ከውሰጥም ከውጭም።

አሁን ለመሰማት የሚከብድ አንድ ዓረፍተ ነገር ይመጣል። ለሁሉም ይሠራል። ለእኔም ጭምር።

መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦ ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋል፤ የእግዚአብሔርንም ክብር አይመጥኑም።[2] ይህ ማለት፦ እግዚአብሔር በመጀመሪያ ለፈጠረው ዓላማ የሚሆን ወይም የሚደርሰ ማንም የለም።

ማንንም አልወቅሰም፤ ማንንም አልከሰም። በመጨረሻ እያንዳንዱ ሰው ከራሱ ፊት ለፊት ይቆማል። ከራሰ መሸሸ አንድ ቀን ያበቃል። ቆም ብሎ ሐቀኛ መሆን ይሻላል፦ መታሰር፣ ባዶነት፣ ትርጉም አልባነት፣ በደል፣ ብቸኝነት፣ መሰበር፣ ዓመፅ፣ ጥፋት አሉ? እነርሱ እንደ ትኩሳት ናቸው። ትኩሳቱ ግን በሽታው አይደለም። በሽታ እንዳለ፣ አንድ ነገር ትክክል እንዳልሆነ ያሳያል።

ከበሰተ ጀርባው በሽታው አለ። ጩኸት እያሰማም። በጸጥታ ይሠራል። ከእርሱ የሚያመልጡበት ደረጃም የለም። ምክንያቱም በደሉ በሌሎች ላይ ወይም ከእኔ ውጭ ብቻ አይደለም። በውሰጤ ነው። በሕይወቴ፣ በታሪኬ፣ በማንነቴ።

አንድ ፈላሰፋ በአንድ ወቅት ሳሊናችንን የፍርድ አዳራሽ ብሎ ጠርቶታል። በውሰጡ ሦስት ድምፆች አሉ፦ ከሳሽ፣ ተሟጋችና ዳኛ። ሦስቱም በውሰጣችን ይናገራሉ። ከሳሹ ያደረግነውን ይዘረዝራል። ተሟጋቹ ሰበብ ይፈልጋል። ዳኛውም ልናመልጠው የማንችለውን

2. ሮሜ 3፥23

ፍርድ ይሰጣል። ይህን የፍርድ አዳራሽ ማንም ሊያብራልን አያስፈልግም። ይዘነው እንዞራለን።

ስለዚህ ቃል ብቻ አይበቃም። አንድ ሰው «ይሁን፣ እንርሳው» ቢለኝ ደግነት ነው። ግን ሌላ ሰው አያደርገኝም። የተፈጸመውንም እንዳልተፈጸመ አያደርገውም። ምንም ሐኪም «ያን ያህል ከባድ አይደለም» በማለት ልጅን አይፈውሰም።

ስለዚህ ሁለት ነገሮች ያስፈልጉናል። ይቅር እንድንባል። በውስጣችን ያለውም እንዲወጣና እንዲያበቃ። አንዱ ያለ ሌላው አይረዳም።

3 እግዚአብሔር በእውነት ምን ዓይነት ነው

ያለ እግዚአብሔር ከዚህ ሁኔታ አንወጣም። ሕልውናችን ያለ እግዚአብሔር ሊታሰብ አይችልም። ብናምንም ባናምንም።

በመጀመሪያ አንድ የተሳሳተ ግንዛቤ።

ሰው ሁሉ ማለት ይቻላል በአእምሮው ሰለ እግዚአብሔር አንድ ምስል አለው። የማያምንም ጭምር። ብዙ ጊዜ የጥብቅ ተቆጣጣሪ ምስል ነው። ሁሉን የሚያይና ምንም የማይረሳ። አንዳንዶች በልጅነታቸው እንዲህ ተምረዋል፦ ደጉ እግዚአብሔር ሁሉን ያያል። ይህ የማጽናኛ ቃል አይመስልም ነበር። የማስጠንቀቂያ ቃል ይመስል ነበር።

ይህ በኢየሱስ መሰቀል ላይ ሲተገበር እንዲህ ይመስላል፦ እግዚአብሔር ቅጣትን ይፈልጋል። ቅጣቱ በእኛ ሳይሆን በእርሱ ላይ እንዲወድቅ ኢየሱስ በመሐል ገባ። ወልድ የተቆጣውን አብ አረጋጋው።

ብዙዎች እንዲህ ሰምተዋል፤ በአብያተ ክርስቲያናትም ጭምር። አንዳንዶች በዚህ ምክንያት ትተው ሄደዋል። ደግ ከመሆኑ በፊት ደም ማየት የሚፈልግን አምላክ ማን ሊታመን ይፈልጋል?

በዚህ ውስጥ እውነት የሆነ ነገር አለ። እግዚአብሔር የምናደርገውን ያያል። ምንንም ዝም ብሎ አያጠፋም። ቀሪው ግን ትክክል አይደለም። በዚህ ምስል የሚጀምር በመጨረሻ ሁሉን በተሳሳተ መንገድ ይረዳል። ይህ ምስል የተዛባ ምስል ነው። ቢያንስ ያልተሟላ ነው።

እግዚአብሔር ፈጽሞ ሌላ ቢሆንስ? በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የመጀመሪያውን እርምጃ የሚወስደው ማን እንደ ሆነ እንመልከት። ፈጽሞ ሰው አይደለም። ሁልጊዜ እግዚአብሔር ነው። አዳም ከተደበቀ በኋላ በእትክልቱ ስፍራ ይፈልገዋል። አብርሃምን ይጠራል። አንድም ትእዛዝ ከመሰጠቱ በፊት ሕዝቡን ከግብፅ ባርነት ያወጣል። በመጨረሻም ልጁን ይልካል።

ከመጽሐፍ ቅዱስ በጣም ከታወቁት ዓረፍተ ነገሮች አንዱ እንዲህ ይላል፦ እግዚአብሔር ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እጅግ ወደደ።[3]

ከአብ ፍቅርን አሰገድዶ የወሰደው ወልድ አይደለም። አብ ሰለ ወደደ ልጁን ሰጠ። በምዕራፍ 1 ያለው ሐኪም ሊረዳ ሰለ ፈለገ እንደ መጣ። ሰለ ተለመነ አይደለም።

ታዲያ እግዚአብሔር እኛ ሌሎችን – በዚያውም እርሱን – የበደልንበትን እንዴት ይይዘዋል? እንደገና ከራሳችን እንጀምር። አንድ ሰው እንደ ጎዳዎት ያሰቡ። በጣም። ሁለት

3. ዮሐንስ 3፥16

ምርጫዎች አሉዎት። ብድሩን ሊመልሱበት ይችላሉ። ወይም ይቅር ሊሉት ይችላሉ።

ይቅር ማለት ምን ማለት ነው? ጉዳቱ ጠፍቷል ማለት አይደለም። ጉዳቱን ለሌላው ከመመለስ ይልቅ እርስዎ ራስዎ ይሸከሙታል ማለት ነው። ይቅር የሚል ይከፍላል። ሁልጊዜ። ይህ የይቅርታ ዋጋ ነው። የሚከፍለውም በደለኛው ሳይሆን ይቅር የሚለው ነው።

ይህ በሰዎች መካከል ያለው ተሞክሮ ነው። ከእግዚአብሔርስ ጋር? የመጽሐፍ ቅዱስ የመጀመሪያው ክፍል በሆነው በብሉይ ኪዳን ለሕዝቡ እንዲህ ይላል፦

> በኃጢአትህ አደከምኸኝ። መተላለፍህን ሰለ ራሴ ብዬ የምደመስስ እኔ፣ እኔ ነኝ።[4]

ሁለቱም ጎን ለጎን ይቆማሉ። ኃጢአት እግዚአብሔርን ያደክመዋል። እርሱ ይሸከመዋል። ይደመስሰዋልም። ሰለ ተገባን አይደለም። እርሱ እንዲህ ሰለ ሆነ ነው እንጂ። ስሕተት ለማግኘት የሚያደባ ዳኛ አይደለም። ይልቁንም ሸክሙን በእርሱ ላይ እንደ ጫንን ከማስተዋላችን ረጅም ጊዜ በፊት አስቀድሞ የሚሸከመው ነው።

ግን ይህ ግማሹ ብቻ ነው። እግዚአብሔር ምንም እንዳልተፈጠረ አያስመስልም። ሁሉን አልፎ የሚያይ አምላክ መልካም አምላክ አይሆንም ነበር። ግድ የለሽ ይሆን ነበር። በአንድ ልጅ ላይ ግፍ ሲፈጸም አንድ ሰው በቁም ነገር እንዲመለከተው እንጠብቃለን። እግዚአብሔር በቁም ነገር ይመለከተዋል። ሁሉንም። እኔ የሠራሁትን ግፍ በእኔ ላይ እንደ ተሠራው ግፍ እኩል በቁም ነገር።

ጥያቄው እግዚአብሔር ኃጢአትን በመሸከምና በመታገሥ ጻድቅ፣ የማያዳላና ወጥ ነው ወይ የሚለው ነው። ያለፈውን፣ የአሁኑንና የሚመጣውን ሁሉ ያቃናል? ይህ ሁሉንም እያንዳንዱንም ይመለከታል። በውድቀታችን – በኃጢአታችን – የደረሰው ጉዳት መቼም ሊስተካከል ይችላል? ሊታሰብ የማይችል ነገር ነው፤ ምናልባት ሊሆን የሚችለው ሊታሰብ በማይችል ተአምር ብቻ ነው።[5]

ይህ ሁሉ በአንድነት ወደ መሰቀል ያደርሰናል። ጥብቅ ብቻ የሆነ አምላክ መሰቀል አያስፈልገውም ነበር። ዝም ብሎ ሊቀጣና ሊበቀል ይችል ነበር። ለዘብተኛ ብቻ የሆነ አምላክም መሰቀል አያስፈልገውም ነበር። ዓይኑን ሊመልስ ይችል ነበር። ያም እኩል አሳዛኝ ይሆን ነበር። እግዚአብሔር ግን ሁለቱም ነው። በደልን በቁም ነገር ይመለከታል። በደለኛውንም ፈጽሞ ይወዳል። እንዲህ ያለ አምላክ ሁለቱም እውነት ሆነው የሚቀሩበትን መንገድ ይሄዳል። በዚህም ውስጥ ልቡ ወዲያና ወዲህ አይከፈልም። እርሱ ፍቅር ነው፤ የሚያደርገውም ፍቅር ነው። ጻድቅና ቅዱስ የሆነ ፍቅር ነው።

መሰቀሉ ይህ መንገድ ነው። መንገዱም የእርሱ ነው። የእኛ አይደለም።

---

4. ኢሳይያስ 43፥24-25
5. ሮሜ 3፥25-26

4 ለምን ደም?

መስቀሉ ደም የፈሰሰበት ጉዳይ ነበር። ደሙንም ማለፍ አንችልም። እንግዳ ቢመስልም። ቢያንሰ በእኛ አካባቢ።

በዕለት ተዕለት ኑሮ ደም እምብዛም አይገጥመንም። በቁስል ጊዜ። ሐኪም ደም ሲወስድ። ወይም ደም ሰንለግሰ። እዚያ በቀላሉ የምንረሳውን አንድ ነገር እንማራለን፦ ደም ሕይወትን ሊያድን ይችላል። የአንዱ ደም ሌላውን በሕይወት ያቆየዋል።

ለመጀመሪያ ጊዜ የእምልኮ ሰብሰባ ላይ የሚገኝ ሰው ሰለ ኢየሱስ ደም የሚናገር መዝሙር ይሰማ ይሆናል። ይገረማልም። ወይም ይጸየፋል። ክርስትና ያለ ደም ለምን አይሆንም? የይቅርታ ቃል ብቻ ለምን አይበቃም?

እንደገና ከራሳችን እንጀምር። አንድ ትንሽ ልጅ በእናቱ ነጭ የጠረጴዛ ልብስ ላይ በማርከሮች ይሥላል። እናቱ ገብታ ታየዋለች። ይቅርም ትለዋለች። ወዲያውኑ፣ ያለ ወቀሳ። ልብሱ ግን አሁንም ቀለም እንደ ያዘ ነው። ይቅርታው እያነጻውም። አንድ ሰው ሊያጥበው ይገባል። የሚያጥበውም ልጁ አይደለም።

በይቅርታና በመንጻት መካከል ያለው ልዩነት ይህ ነው። ይቅርታ፦ «አልቆጥርብህም» ይላል። መንጻት፦ «ጠፍቷል» ይላል። ሁለቱም ያስፈልጉናል። በምዕራፍ 2 ኃጢአት እንደ በሽታ በውስጣችን እንዳለ አይተናል። ስለዚህ «ይሁን፣ እነርሳው» የሚል ብቻ አያስፈልገንም። የሚፈውስ ያስፈልገናል።

ከእግዚአብሔርስ ጋር? ይህንን ከኢየሱስ ረጅም ጊዜ በፊት ለሕዝቡ ለእስራኤል አስተምሮታል። ለእኛ እንግዳ በሆነ ቋንቋ። በዚያን ጊዜ ሁሉም ይረዳው ነበር። የመሥዋዕት ቋንቋ ነው።

በደል የፈጸመ እስራኤላዊ እግዚአብሔር ወደሚኖርበት ሰፍራ ወደ መቅደሱ እንስሳ ያመጣ ነበር። እጁን በእንስሳው ራስ ላይ ይጭን ነበር። ይህም፦ ይህ እንስሳ አሁን እኔን ይወክላል ማለት ነበር። ከዚያም ይታረድ ነበር። ካህኑ ደሙን ወስዶ ወደ መሠዊያው ያቀርበው ነበር። ዋናው ነገር ደሙ ነበር። መግደሉ አይደለም። ደሙ።

ለምን? ምክንያቱም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ደም ሕይወትን ይወክላል። በሙሴ ሕግ ውስጥ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦

ሕይወት በደም ውስጥ ነው፤ እንዲሸፍናችሁም በመሠዊያው ላይ ሰጠኋችሁ።[6]

በዚህ ዓረፍተ ነገር ውስጥ ብዙ ነገር አለ። ደሙን የሚሰጠው እግዚአብሔር ነው። አበዳሪ ገንዘቡን እንደሚጠይቅ አይጠይቀውም። ሐኪም መድኃኒት እንደሚሰጥ ይሰጠዋል። ደሙ የሚያደርገውም «መሸፈን» ይባላል። በበደሉ ላይ ይዘረጋል። በዚያው ጊዜም ያሰወግደዋል።

ይህ እንግዳ ቋንቋ ምን ይላል? ሦስት ነገሮችን፦

በደል ከባድ ነው።

ሕይወት ያሰከፍላል።

ይህንንም ሕይወት የሚሰጠው እግዚአብሔር ነው።

እንሰሶቹ ግን ምሳሌ ብቻ ነበሩ። በግ ለምን እንደሚሞት አያውቅም። ምንም ሰለማይረዳ ምንም ሊሸከም አይችልም። መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ የእንሰሳት ደም በደልን ሊያሰወግድ እንደማይችል ይናገራል።[7] የትምህርት ዓይነት ነበር። እግዚአብሔር አንድ ቀን በእውነት የሚያደርገውን በዚህ አሰቀድሞ አሰታወቀ።

ከዚያም አደረገው። በእንሰሳ አይደለም። የሚያደርገውን በሚያውቅ ሰው። በፈቀደው። እርሱም የእግዚአብሔር የራሱ ልጅ ነበር። እዚህ እግዚአብሔር የሌላውን ደም አልወሰደም። የራሱን ሰጠ።

ሰለዚህ ደም። እግዚአብሔር ደም ማየት ሰለሚፈልግ አይደለም። በደል ሕይወት ሰለሚያሰከፍል ነው እንጂ። እግዚአብሔርም ያ ሕይወት የራሱ እንዲሆን ሰለ ወሰነ። አብና ወልድ በዚህ ሥራ ፍጹም አንድ ናቸው።

6. ዘሌዋውያን 17፥11
7. ዕብራውያን 10፥4

5 ኢየሱስ ራሱ የተናገረው

ኢየሱስ ራሱስ? የሚመጣበትን ያውቅ ነበር?

አንድ ሰው ያለ ጊዜው ሲሞት ወደ ኋላ የቀሩት ብዙ ጊዜ እንዲህ ብለው ይጠይቃሉ፦ ገምቶት ነበር? አሁን ብቻ የምንረዳው አንድ ነገር ተናግሮ ነበር? አንዳንድ ጊዜ ደብዳቤ ይገኛል። ወይም በዚያን ጊዜ ችላ የተባለ አንድ ዓረፍተ ነገር ይታወሳል።

በኢየሱስ ዘንድ ሌላ ጥርጣሬ ቶሎ ይመጣል፦ ለሞቱ ትርጉም የተሰጠው በኋላ ነው ይባላል። አንድ ሰባኪ ከልክ አለፈ። ባለ ሥልጣናቱ ከመንገዳቸው አስወገዱት። ወዳጆቹም ከዚያ በኋላ ትርጉም በሌለው ሞት ውስጥ ትርጉም ፈለጉ። እንዲህ ያለ ነገር ይከሰታል። ሰዎች ሲያዝኑ ይህን ያደርጋሉ።

ዘገባዎቹ ግን ሌላ ይላሉ። ኢየሱስ ሞቱ ከመምጣቱ በፊት ስለ እርሱ ተናግሯል። በተደጋጋሚ። ለሞቱም ራሱ በትክክል የቤዛነትን ትርጉም ሰጠው።

ሦስት ጊዜ ለወዳጆቹ ወደ ኢየሩሳሌም እንደሚሄድና በዚያ መሞት እንዳለበት ነገራቸው። እንዳለበት። ሊሰሙት አልፈለጉም። ከእነርሱ አንዱ ጴጥሮስ አጥብቆ ተቃወመው። ኢየሱስ ግን በዚያው ጸና።

አንድ ጊዜ ራሱን ሐኪም ብሎ ጠራ። ከተጠሉት ቀረጥ ሰብሳቢዎችና መጥፎ ሰም ካላቸው ሌሎች ሰዎች ጋር በማዕድ በመቀመጡ ወቀሱት። እርሱም እንዲህ ብሎ መለሰ፦

ሐኪም የሚያስፈልጋቸው ሕመምተኞች ናቸው እንጂ ጤነኞች አይደሉም።[8]

ወደ እነማን እንደ መጣ ያውቅ ነበር። ለምንም እንደ መጣ ተናገረ፦

የሰው ልጅ ሊያገለግልና ነፍሱን ለብዙዎች ቤዛ አድርጎ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም።[9]

የሰው ልጅ – ኢየሱስ ራሱን እንዲህ ብሎ ይጠራ ነበር። ቤዛ እስረኛን ነጻ የሚያወጣ ገንዘብ ነው። ከምርኮ፣ ከባርነት። በዕዳ ከተያዘ ሕይወት። ኢየሱስ እንዲህ ይላል፦ ሕይወቴ ዋጋው ነው። ነጻ የምትወጡትም እናንተ ናችሁ።

በመጨረሻው ምሽት ከወዳጆቹ ጋር የፋሲካን እራት በላ። በዚህ በዓል እስራኤል እስከ ዛሬ ከግብፅ መውጣቱን ያስታውሳል። እንጀራን እንሥቶ ቆረሰና፦ ይህ ስለ እናንተ የሚሰጥ

8. ማርቆስ 2፥17
9. ማርቆስ 10፥45

ሥጋዬ ነው አለ። የወይን ጠጅ ያለበትን ጽዋ አነሥቶ፦ ይህ ለኃጢአት ይቅርታ ስለ ብዙዎች የሚፈስ ደሜ ነው አለ።[10]

አልተረዱትም። በኋላ ነው የተረዱት። እርሱ ግን ከመፈጸሙ በፊት ተናግሮታል። እንደሚሞት ያውቅ ነበር። ስለ እነማን እንደሚሞት ያውቅ ነበር። ለምንም እንደሚሞት ያውቅ ነበር።

ከዚያም በደብረ ዘይት ተራራ ግርጌ በጌቴሴማኒ አትክልት ውስጥ ያ ሌሊት መጣ። በዚያ ምን እንዳስከፈለው እናያለን። ከወዳጆቹ ሦስቱን ይዞ ሄደ። ነፍሱ እስከ ሞት ድረስ እጅግ እንዳዘነች ነገራቸው። ከዚያም በምድር ላይ ወድቆ ጸለየ፦

አባት ሆይ፣ ሁሉ ይቻልሃል። ይህን ጽዋ ከእኔ አርቅ። ነገር ግን አንተ የምትወደው እንጂ እኔ የምወደው አይሁን።[11]

ጽዋው ጥንታዊ ምሳሌ ነው። በእስራኤል ነቢያት ዘንድ ጽዋ እግዚአብሔር ለሰው እንዲጠጣ የሚሰጠው ነው። የእርሱ ድርሻ። የእርሱ ዕጣ ፈንታ። አንዳንድ ጊዜ በረከት ነው። አንዳንድ ጊዜ ለሰው ሊሰፈርለት የሚችል እጅግ ከባዱ ነገር ነው። ኢየሱስ በጽዋው ውስጥ ያለውን አየ። ከእርሱ እንዲያልፍ ለመነ። ከዚያም ጠጣው።

ስለዚህ ሳያውቅ ወደ ሞቱ አልተደናቀፈም። የሚመጣውን አየ። እንዲተርፍ ለመነ። ቢሆንም ሄደ። በምዕራፍ 7 ወደዚህ እንመለሳለን።

በመስቀል ላይ፣ ከመሞቱ ጥቂት ቀደም ብሎ፣ አንድ ተጨማሪ ቃል ተናገረ። በግሪክ አንድ ቃል ብቻ ነው። በአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስም እንዲሁ አጭር ነው፦ ተፈጸመ።[12] ይህ «አበቃ» ማለት አይደለም። ይልቁንም «ተሠራ» ማለት ነው። ተልእኮው ተፈጽሟል።

10. ሉቃስ 22፥19፤ ማቴዎስ 26፥28
11. ማርቆስ 14፥34-36
12. ዮሐንስ 19፥30

6 ሦስት ከባድ ዓረፍተ ነገሮች

አሁን ነገሩ ይከብዳል።

ቀሰ ብለው ሊያነቧቸው የሚገቡ ሦስት ዓረፍተ ነገሮች።

ሁለት ጊዜ ሊያነቧቸው የሚገቡ ዓረፍተ ነገሮችን ያውቃሉ። ከሐኪም የመጣ የምርመራ ውጤት። ከመንግሥት መሥሪያ ቤት የመጣ ደብዳቤ። ያነቡታል፣ ያሰቀምጡታል፣ እንደገና ያነቡታል። ብዙ ነገር በእርሱ ላይ የተመካ ሰለ ሆነ።

ሰለ ኢየሱስ ሞትም እንደዚህ ያሉ ዓረፍተ ነገሮች አሉ። የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ሞቱን በጥቂት ዓረፍተ ነገሮች ጠቅልለውታል። ከእነርሱ ሦስቱ በተለይ ከባድ ናቸው። ብዙ ነገር ሰለሚሸከሙ ከባድ ናቸው። በቀላሉም በተሳሳተ መንገድ ሰለሚተረጎሙ ከባድ ናቸው።

የመጀመሪያው ዓረፍተ ነገር፦ መጻሕፍት እንደሚሉ ክርስቶስ ሰለ ኃጢአታችን ሞተ።[13]

ይህ ሰለ መስቀሉ ያለን እጅግ ጥንታዊው ዓረፍተ ነገር ነው። ጳውሎስ ከክርስቶስ ልደት በኋላ 55 ገደማ በቆሮንቶስ ላሉ ክርስቲያኖች ጻፈው። ከእርሱ በፊት ክርስቲያኖች ከነበሩት እርሱ ራሱ እንደ ተቀበለውም ይናገራል። ሰለዚህ ዓረፍተ ነገሩ የመጣው ከመስቀሉ በኋላ ከነበሩት የመጀመሪያ ዓመታት ነው። ከብዙ ትውልዶች በኋላ ማንም የፈጠረው አይደለም።

ሰለ ኃጢአታችን። በጠላቶቹ ምክንያት አይደለም። ለእኛ እርእያ ለመሆን አይደለም። ይልቁንም፦ ሰለ ኃጢአታችን። ሞቱ በምዕራፍ 2 ከተጻፈው ጋር ግንኙነት አለው። በውስጣችን ካለው በሽታ ጋር። ከእነግዲህ ልናስተካክለው ከማንችለው ጋር።

መጻሕፍት እንደሚሉ። ይህ ማለት፦ በእሰራኤል መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አስቀድሞ እንዲህ ተጽፎ ነበር ማለት ነው። የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች መስቀሉን አዲስ አልፈጠሩትም። በዚያ እንደገና አገኙት። እጅግ በግልጽ የሚገኘው ከብዙ መቶ ዓመታት በፊት በነበረ አንድ መዝሙር ውስጥ ነው። ሰለሚናቅ፣ መከራ ሰለሚቀበልና ሰለሚሞት ሰለ እግዚአብሔር አገልጋይ ይናገራል። እንዲህም ይላል፦

ደዌያችንን ተሸከመ። ሰለ መተላለፋችን ቆሰለ። እግዚአብሔር የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ አኖረ።[14]

---

13. 1 ቆሮንቶስ 15፥3
14. ኢሳይያስ 53፥4-6

እዚህ ያለው ቃል በእርግጥ በሽታ ማለት ነው። «የኃጢአት ደዌ» ነው። ነቢዩ ሌሎቹ የታመሙበትን ወደ ራሱ የሚወሰድ አንድ ሰው ያያል። በልጁ አልጋ አጠገብ እንዳለው ሐኪም።

የእስራኤል መጽሐፍ ቅዱስ የነጻነት ታሪኮች ወደ መስቀሉ አስቀድመው ያመለክታሉ። በዚያ በአንድ ሕዝብ ላይ የሆነው እዚህ ለሰዎች ሁሉ ይሆናል።

ሁለተኛው ዓረፍተ ነገር፦ እኛ በእርሱ የእግዚአብሔር ጽድቅ እንድንሆን ኃጢአትን ያላወቀውን እግዚአብሔር ስለ እኛ ኃጢአት አደረገው።[15]

ይህ ከሦስቱ እጅግ ከባዱ ነው። ቁራጭ በቁራጭ ሊያነቡት ይገባል።

ኃጢአትን ያላወቀውን፦ ኢየሱስ የራሱ በደል አልነበረበትም፤ ከዓመፅ ጋርም ፈጽሞ አልተባበረም። ኃጢአት አደረገው፦ እግዚአብሔር ኃጢአት ባለበት ቦታ አቆመው። እኛ ካለንበት ማንነት ጋር አንድ አደረገው። ኃጢአተኛ አደረገው ማለት አይደለም። ይልቁንም ጉዳያችንን ሙሉ በሙሉ አሳልፎ ሰጠው ማለት ነው። ከዚያም ግቡ፦ የእግዚአብሔር ጽድቅ እንድንሆን። በእርሱ።

ጽድቅ እዚህ ምንም ስሕተት የሌለበት መሆን ማለት አይደለም። ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም መሆን ማለት ነው። እንደገና የእርሱ መሆን።

ይህ ልውውጥ ነው። እርሱ የእኛን ይቀበላል። እኛ የእርሱን እንቀበላለን። ነገር ግን ሁለት እንግዶች አንድን ነገር ወዲያና ወዲህ እንደሚያቀባብሉበት እንደ ገበያ ልውውጥ አይደለም። በእርሱ ውሰጥ የሚሆን ልውውጥ ነው። ወደ ውሰጥ እንወሰዳለን። ወደ መስቀል ሞቱ። ወደ ትንሣኤ ሕይወቱም።

ጳውሎስ አንድ ጊዜ ለአንድ ወዳጁ አጭር ደብዳቤ ጻፈ። የወዳጁ ባሪያ ኮብልሎ ነበር። ሰሙ አናሲሞስ ነው። ምናልባት አንድ ነገር ይዞ ሄዶ ይሆናል። ጳውሎስ አወቀው፤ መልሶም ላከው። እንዲህም ጻፈ፦ አንዳች ዕዳ ካለበት በእኔ ሂሳብ ላይ ጻፈው። እኔ እከፍላለሁ።[16] እዚህ ማንም ሰለ ቅጣት አያሰብም። አንዱ ሰለ ሌላው ኃላፊነት ይወሰዳል። መጽሐፍ ቅዱስ ሰለ ኢየሱስም እንዲሁ ይናገራል።

ሦስተኛው ዓረፍተ ነገር፦ ኃጢአታችንን በገዛ አካሉ በእንጨት ላይ ተሸከመ።[17]

ይህን ዓረፍተ ነገር ከምዕራፍ 1 አስቀድመው ያውቁታል። ቦታውን ይጠራል። በገዛ አካሉ። በእንጨቱ ላይ፣ በመስቀሉ ላይ። በሐሳብ አይደለም፤ በስማይ የሆነ ቦታ አይደለም። በአንድ የተወሰነ ቀን፣ በአንድ የተወሰነ ግንድ ላይ፣ ሊደማ በሚችል አካል።

---

15. 2 ቆሮንቶስ 5፥21
16. ፊልሞና 1፥18-19
17. 1 ጴጥሮስ 2፥24

ድርጊቱንም ይጠራል፦ ተሸከመ። ለዚህም ከመሥዋዕት ቋንቋ የተወሰደ አንድ ተጨማሪ ምሳሌ አለ። በዓመት አንድ ጊዜ፣ በታላቁ የማስተሰረያ ቀን (ዮም ኪፑር)፣ ካህኑ ሁለቱንም እጆቹን በሕያው አውራ ፍየል ራስ ላይ ይጭን ነበር። የሕዝቡን በደል ሁሉ በእርሱ ላይ ይናዘዝ ነበር። ከዚያም ፍየሉን ወደ ምድረ በዳ ይነዱት ነበር። በደሉን ተሸክሞ ወስደው። ወደማይመለስበት ሰፍራ።[18]

በሦስተኛው ዓረፍተ ነገር ውስጥም በትክክል ይህ ቃል ይገኛል፦ ተሸከመ። ተሸክሞ ወስደ። ኢየሱስ በደሉን ተሸክሞ ወደ ውጭ እንደሚወስደው ፍየል ነው። በዚያው ጊዜም ደሙ የሚያነጻ መሥዋዕት ነው። ሁለቱም በአንድ አካል።

ዓረፍተ ነገሩ ይቀጥላል፦ ለኃጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር። እዚህ «የተሻለ እንዲሰማን» አይልም። «በሌላ መንገድ እንድንኖር» ይላል። የኢየሱስ ሞት ለእኛ የተደረገ ነገር ብቻ አይደለም። በእርሱ በኩል ከእኛ ጋርና በውስጣችንም አንድ ነገር ሊሆን ይገባል።

ከዚያም አስቀድመን የምናውቀው ዓረፍተ ነገር ይመጣል፦ በቁስሉ ተፈወሳችሁ። ሞቱ ሕይወታችን ነው።

18. ዘሌዋውያን 16፥21-22

7 ሞቱ እንዴት ያድነናል

አሁን መልሰ ይመጣል። ወይም ቢያንሰ የመልሰ ሙከራ።

አንድ ሰው ያጣ ሰው እንዲህ ብሎ ይጠይቃል፦ ለምን? ለምን እርሱ? ለምን እንዲህ? ብዙውን ጊዜ መልሰ አይገኝም። ሞት ትርጉም የለሽ ሆኖ ይቀራል።

ሰለ ኢየሱሰ ግን በሌላ መንገድ እንጠይቃለን። «ለምን ሞተ?» ብቻ አይደለም። ይልቁንም፦ «በሞቱ ምን ሆነ?» ይህ ከምዕራፍ 1 ሦስተኛው ጥያቄ ነው። በአምሰት እርምጃዎች ለመቅረብ እሞክራለሁ።

በመጀመሪያ፦ በራሱ ላይ ወሰደው።

ኢየሱሰ በአደጋ ውሰጥ አልወደቀም። ገብቶበታል። በኢየሩሳሌም የሚጠብቀውን ያውቅ ነበር። ቢሆንም ወደዚያ ሄደ። ከመሞቱ በፊት በነበረው ሌሊት ከእርሱ እንዲያልፍ ጸለየ። ከዚያም፦ እኔ የምወደው ሳይሆን እንተ የምትወደው ይሁን አለ።[19]

ከዚያ በኋላ የመጣውን ያደረጉት ሰዎች ናቸው። በአንድ ወዳጅ መከዳት። ከመጀመሪያው የተወሰነ ፍርድ። ግርፋት፣ መዘባበት፣ ግድያ። ከሰማይ የወረደ መብረቅ አይደለም። የሰው እጆች። ቢሆንም መጽሐፍ ቅዱሰ እንዲህ ይላል፦ ይህ በትክክል የእግዚአብሔር መንገድ ነበር። እግዚአብሔር ልጁን አሳልፎ ሰጠ።[20] ሁለቱም እውነት ናቸው። ሰዎች አደረጉት። እግዚአብሔር እንዲህ ሰለ ፈለገ እንዲሆን ፈቀደ። ምዕራፍ 3 የተናገረው ሊታሰብ የማይችል ተአምር በዚህ እንዲፈጸም ነበርና።

ኢየሱሰ በዚያ የተቀበለው ያለ እግዚአብሔር ያለ ዓለም መንገዱን ሲሄድ የሚሆነው ነው። ዘሩ ይበቅላል። ውሸት፣ ዓመፅ፣ ግፍ፣ ሞት። ይህ የበደልና የኃጢአት መከር ነው። እርሱ በገዛ እካሉ ሰበሰበው። የእርሱን መከር አይደለም። የእኛን።

ሁለተኛ፦ ሊሸከመው የቻለው የእርሱ ሰላልነበረ ነው።

እዚህ በምዕራፍ 1 ያለው የሐኪሙ ምሳሌ ይረዳል። ሐኪሙ በሽታውን ከልጁ ላይ ለምን ሊወሰድ ቻለ? ሐኪሙ ራሱ በሽታው ሰላልነበረበት። ጤነኛ ሆኖ ከውጭ መጣ። ራሱ የሚታፈን ሐኪም ለአንድም ልጅ ትንፋሽ ሊሰጥ አይችልም።

እዚህም እንዲሁ ነው። ኢየሱሰ የራሱ በደል አልነበረበትም። መልሶ ሊወሰደው የሚገባ ቃል አልነበረም። በኃይል የዘጋው በር አልነበረም። ሰለዚህ የእኛን ሊሸከም ቻለ። ጻድቁ

19. ማርቆሰ 14፥36
20. ሮሜ 8፥32፤ የሐዋርያት ሥራ 2፥23

ሰለ ዓመፀኞች።[21] ይሸከማል። በደላችንን ይወሰዳል። ሙሉ በሙሉ ከኃጢአተኞች ጎን ይቆማል። ይህ በመስቀል ላይ ይሆናል። ይህ በእነዚያ ሰዓታት በእርሱ ላይ ምን አደረገ?

ሦስተኛ፦ ወደ ሞቱ ውሰጥ ይዞት ገባ።

ሞት መሆን ለምን አሰፈለገ?

ምዕራፍ 2ን ያሰታውሱ። ኃጢአቱ በሌሎች ላይ ወይም ከእኔ ውጭ ብቻ አይደለም። በውሰጤ ነው። በሕይወቴ። ኃጢአት፣ በአንድ ሕይወት ውሰጥ የተቀመጠው ይህ ገዳይ በሽታ፣ የሚያበቃው ያ ሕይወት ሲያበቃ ብቻ ነው። ሰለዚህ እንደ ሂሳብ ዝም ብሎ ሊሰረዝ አይችልም። ሂሳብን መቅደድ ይቻላል። ሕይወትን ግን አይቻልም።

ኢየሱሰ ኃጢአታችንን ወደ ሕይወቱ ወሰደ። ሐኪሙ የልጁን በሽታ እንደ ወሰደ። ይህንም ሕይወት ለሞት አሳልፎ ሰጠ። በደሉና በሽታችን ወደሚገባቸው ቦታ አብረው ሄዱ። ፍየሉ ኃጢአቶቹን ወደ ምድረ በዳ፣ ወደ ሞት ምድር ተሸክሞ እንደ ወሰደ። በዚያም ቀረ።

መጽሐፍ ቅዱሰ በዚህ ጠንካራ ዓረፍተ ነገር ይናገረዋል፦

እግዚአብሔር በልጁ ሥጋ ኃጢአትን ኮነነ (ፈረደበትም)።[22]

ልጁን አይደለም። ኃጢአትን። ኃጢአት ፍርዱን የተቀበለችው እርሱ ተሸክሞ በወሰዳት ቦታ ነው። ይህ በምዕራፍ 3 ለተነሣው ጥያቄ መልሰ ነው። እግዚአብሔር ዓይኑን አይመልሰም። ኃጢአትን ይፈርድባታል። ኃጢአተኛውንም ያድነዋል። በዚህ መንገድ ሰለ እኛ መሞቱ ወደ ሕይወት የሚያሰገባ በር ይሆናል።

ደሙሰ? በመጽሐፍ ቅዱሰ ውሰጥ ደም አሳልፎ የሚሰጥን ሕይወት ይወክላል። ጭካኔን አይደለም። «ሕይወቴን ሰለ እናንተ እሰጣለሁ» ይላል።

የኃጢአት ደመወዝና ውጤት ሞት ነው። የሕይወት ራሰ ከዘላቂው፣ ከዘላለማዊው ሞት ሊያድነን በእኛ ፋንታ ይሞታል።

አራተኛ፦ ሞት ሊይዘው አልቻለም።

የሐኪሙ ምሳሌ እዚህ ያበቃል። ሐኪሙ በበሽታው ሞተ፤ በዚያም ቀረ። በኢየሱሰ ዘንድ እንዲህ ሆኖ አልቀረም። እርሱ ራሱ ፍጹም መልካምና ጻድቅ ነበር። የሌሎች ኃጢአት የሚያበቃበት ሞት እርሱን ለመያዝ መብትም ምክንያትም የለውም። ከሦስት ቀን በኋላ መቃብሩ ባዶ ነበር። ይህ ባይሆን ኖሮ ሌላው ሁሉ መልካም ምሳሌ ብቻ በሆነ ነበር። በዚህ ግን መዳን ነው። የሚቀጥለው ምዕራፍ ሰለዚህ ይናገራል።

አምስተኛ፦ ሞቱ እንደ ሞታችን ይቆጠራል።

---

21. 1 ጴጥሮሰ 3፥18
22. ሮሜ 8፥3

አሁን ጉዳዬን የእኔ ጉዳይ የሚያደርገው እርምጃ ይመጣል። መጽሐፍ ቅዱስ «ስለ እኛ ሞተ» ብቻ አይልም። «ከእርሱ ጋር ሞተናል» ይላል።[23] ይህ የሃይማኖት አባባል አይደለም። እንዲህ ማለት ነው፦ በሞቱ ያበቃው የእኔ የታመመና ኃጢአተኛ ማንነት ነበር። ያን ጊዜ የነበርሁት ሰው በዚያ በመስቀሉ ላይ ሞተ፤ ከእርሱም ጋር ወደ መቃብር ተቀበረ። ከመቃብሩ የወጣውም ልሆን የሚገባኝ ነገር መጀመሪያ ነው። እሮጌው አልፏል፤ አዲስ ሆኗል።[24]

ስለዚህ ይህ ሞት ሊዘለል የማይገባው አንድ ትንሽ ቃል አለው፦ «ከ… ጋር»። ስለ እኛ ብቻ አይደለም። ከእርሱ ጋር። እርሱን የሚይዝ ከእርሱ ጋር ይወሰዳል። ከእርሱ ጋር ወደ ውሰጥ፣ በደልና ኃጢአት ወደሚቀሩበት ወደ ሞቱ ይገባል። ከእርሱም ጋር ወደ ውጭ፣ ከእንግዲህ ወደሌሉበት ወደ ሕይወቱ ይወጣል።

ይህ ግንኙነት ከ2000 ዓመት በፊት በሆነ አንድ ክሰተት እንዴት ሊፈጸም እንደሚችል ልናገር አልችልም። እዚህም ይህ ይሠራል፦ ይህ የእግዚአብሔር መንገድና መፍትሔ ነው።

ይህ ምን ማለት ነው።

ከእንግዲህ ሊያሰተካክሉት የማይችሉትን ያስቡ። ይህን የማሳሰብዎ መጥፎ እንዲሰማዎ አይደለም። እንዳልተፈጸመ አልሆነም። ይህን የሚል የለም። ነገር ግን ተሸክሞ ተወሰዷል። ሊሸከመው በቻለው። ፈጽሞ ወደማይመለሰበት ሰፍራ።

እርሰዎስ?

ያ ነገር በውሰጡ የሚኖርበት ሰው ከእንግዲህ አይደሉም። ከእርሱ ጋር በሞት በኩል አልፈዋል። ይህ ሰሜት አይደለም። እግዚአብሔር ያጸናው እውነታ ነው። በዚህ የእግዚአብሔር እውነት ላይ መቆም ይችላሉ።

ልገልጸው የማልችለው ቀሪ ነገር አለ? አዎን። አንድ ሕይወት ሌሎችን ሕይወቶች በሞት በኩል እንዴት ይዞ ሊያልፍ እንደሚችል ምሥጢር ሆኖ ይቀራል። ይህ ለኢየሱሰ በውሰጡ ጥልቀት ምን ማለት እንደ ነበረም እንዲሁ። ነገር ግን ቀን፣ ቦታና ባዶ መቃብር ያለው ምሥጢር ነው።

እዚህ ላይ ማለት የምችለው ይህን ብቻ ነው፦ ኢየሱሰ ሆይ፣ አመሰግንሃለሁ፤ አመሰግንሃለሁ!

23. ሮሜ 6፥4፤ 2 ቆሮንቶሰ 5፥14
24. 2 ቆሮንቶሰ 5፥17

8 ትንሣኤ ለምን የታሪኩ አካል ነው

ዓርብ ዕለት ሞተ።

እሑድ ዕለት መቃብሩ ባዶ ነበር።

በመቃብር አጠገብ የቆመ ሰው ይህን ሰሜት ያውቀዋል። እዚህ አንድ ነገር አብቅቷል። ለዘለቄታው። አበባ ማምጣትና ሻማ ማብራት ይቻላል። ነገር ግን የመጨረሻውን ቃል የሚናገረው ሞት ነው። ቢያንስ እንዲህ ይመስላል።

የኢየሱስ ታሪክ ዓርብ ዕለት ያበቃ ነበር ብለው ያስቡ። አንድ መልካም ሰው ተገደለ። ወዳጆቹ የሚቀጥሉት እነርሱ እንዳይሆኑ ፈርተው ተደበቁ። መቃብሩ በከባድ ድንጋይ ተዘግቶ ይጠበቅ ነበር።

ያኔ ልብ የሚነካ ምሳሌ ይኖረን ነበር። ሰለ እምነቱ የሞተ አንድ ሰው። በመስቀል ላይ ሳለ እንኳ ለገዳዮቹ የጸለየ አንድ ሰው። ሰው ሊያደንቀው ይችል ነበር። እርሱን ለመምሰል ሊሞክር ይችል ነበር። ነገር ግን ማንም አይድንም ነበር። በምዕራፍ 1 እንዳለው ሐኪም በሆነ ነበር፦ በሽታውን ወደ ራሱ ወሰደ፤ በሽታውም ገደለው።

ጳውሎስ ያለ ማወላወል ይናገረዋል፦

ክርስቶስ ከሙታን ካልተነሣ እናንተ ገና በኃጢአታችሁ ውስጥ ናችሁ።[25]

ገና በኃጢአታችሁ ውስጥ። ያኔ መቃብሩ በደሉ የቀረበት ሰፍራ አይሆንም ነበር። እርሱም ደግሞ የቀረበት ሰፍራ ብቻ ይሆን ነበር። ያኔ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጻፈው ሁሉ ከንቱ በሆነ ነበር።

የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ያልተሰማ ነገር ይናገራሉ። ሞቶ አልቀረም ይላሉ። በሦስተኛው ቀን መቃብሩ ባዶ ነበር ይላሉ። ሴቶች ማልደው በማለዳ እንዲህ አገኙት። ለወዳጆቹም ተገለጠ ይላሉ። እንደ መንፈስ አይደለም። ከእነርሱ ጋር እንደሚበላና ቁስሎቹ ሊዳሰሱ እንደሚችሉ ሰው።

ይህ እውነት ቢሆንስ? ያኔ ለጥያቄያችን ቢያንስ ሦስት ነገሮችን ያመለክታል።

በመጀመሪያ፦ እግዚአብሔር «አዎን» ብሏል። ዓርብ ዕለት ለሆነው «አዎን»። እግዚአብሔር ከሙታን ካሰነሣው፣ ሞቱ እግዚአብሔር በኋላ የጠገነው ዕድለ ቢስ አደጋ አልነበረም። ያኔ ሁሉም ነገር መንገዱ ነበር፤ እግዚአብሔርም አረጋገጠው። አንድ ጥንታዊ ዓረፍተ ነገር ሁለቱንም በአንድ ትንፋሽ ይናገራል፦ ሰለ በደላችን አልፎ ተሰጠ፤

25. 1 ቆሮንቶስ 15፥17

በእግዚአብሔር ፊት ጻድቃን ሆነን እንድንቆምም ከሙታን ተነሣ።[26] ሞቱ በደልን ያስወግዳል። ትንሣኤው፦ «ይህ ለዘመናት ሁሉ የጸና ነው» ይላል።

ሁለተኛ፦ በደሉ በመቃብር ውስጥ ቀረ። እርሱ ግን አልቀረም። ይህ በደሉ ከእንግዲህ እንደሌለ የሚያሳይ ምልክት ነው። አንድ ነገር ገና ያልተፈጸመ ቢሆን ኖሮ ሞት እርሱን ሊያስቀረው በተፈቀደለት ነበር።

አጭር ማብራሪያ፦ «በደሉ በመቃብር ውስጥ ቀረ» የሚለው ምሳሌ ነው። ተጠናቋል፣ ተወግዷል፣ ከእንግዲህ የለም ማለት ነው።

ሦስተኛ፦ ሕያው ነው። ስለ እኛ የሞተው ያለፈ ታሪክ አይደለም። እዚህ አለ። ዛሬ። ለዘላለም። ሰዋዊ በሆነ፣ በማይሞት የትንሣኤ አካል ወደ እግዚአብሔር ሄዷል። ከዚያም ተመልሶ ይመጣል።

በነገራችን ላይ የዲፍቴሪያ ታሪክ ቀጠለ። በ19ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ መድኃኒት ተገኘ። የተገኘውም ከፈረሶች ደም ነበር። የበሽታው መርዝ ተሰጥቷቸው ነበር፤ በመጀመሪያ ጥቂት፣ ከዚያም ብዙ። ፈረሶቹ መርዙን አሸነፉት። በደማቸውም ውስጥ አሁን ልጆቹን ያዳነው ነገር ነበር። በዚህ መንገድ በሺህ የሚቆጠሩ ልጆች በሕይወት ተርፈዋል።

ምሳሌ ሁሉ ጉድለት አለው፤ ይህም እንዲሁ። ነገር ግን አንድ ነገር ያሳያል። በሽታውን አልፎ ያሸነፈው ሰው ሕይወቱ ሌሎችን ሊፈውስ ይችላል። ኢየሱስ የዓለምን በሽታ ወደ ራሱ ወሰደ፤ ሞትንም አሸነፈ። ሕይወቱ አሁን ለእኛ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦

> በሕይወቱ እንድናለን።[27]

ክፋት አሁንም አለ። በሽታውም፣ ሞትም አሉ። ነገር ግን መድኃኒቱ ተገኝቷል። የእነርሱ ፍጻሜ የተወሰነ ነው።

26. ሮሜ 4፥25
27. ሮሜ 5፥10

9 የምሥራቹ

እኔስ?

ከዚህ ምን አገኛለሁ?

ይህን መጽሐፍ እስከዚህ ድረስ አንብበዋል። ምናልባት በጉጉት። ምናልባት በጥርጣሬ። ምናልባት በሁለቱም። ይህ ከምዕራፍ 1 የመጨረሻው ጥያቄ ነው፦ ይህ ወደ እኔ እንዴት ይደርሳል? አንድ ሰው ከሁለት ሺህ ዓመት በፊት ሞተ፤ ከሙታንም ተነሣ። ከዚህ ጋር ምን ግንኙነት አለኝ?

ዝም ብዬ እስከምመለከት ድረስ ምንም። ራሴን ለእርሱ አሳልፌ እንደ ሰጠሁ ሁሉም።

በጠና የታመመና በዚያው ጊዜ በፍርድ ቤት ፊት ተከሶ የቆመ አንድ ሰው ያስቡ። ሁለት ነገሮች ይጎድሉታል፦ ነጻ መለቀቅና ጤና። ነጻ ሊለቀቅ ይችላል፤ ግን ታሞ ይቀራል። ሊፈወስ ይችላል፤ ግን ተከሶ ይቀራል። ሁለቱም ያስፈልጉታል።

ሁኔታችን እንዲህ ነው። ይህን በምዕራፍ 2 አይተናል። ይቅርታ ያስፈልገናል። በውስጣችን ያለው በሽታ እንዲያበቃም ያስፈልገናል። መሰቀሉ፣ ወይም ይልቁን የተሰቀለው፣ ሁለቱንም ይሰጣል። ነገር ግን ሳንቲም እንደሚጣልበት ማሸን አይደለም። ወደ አልጋው እንደሚቀርብ ሐኪም ይሰጠዋል። መገናኘት ያስፈልጋል።

ሕመምተኛው ምን ማድረግ አለበት? በምዕራፍ 1 ያለውን ልጅ ያስቡ። ዝም ብሎ ከመቆየትና ሐኪሙ እንዲሠራ ከመፍቀድ በቀር ምንም ማድረግ አልቻለም። ሐኪሙ የሚያደርገውን መረዳት አላስፈለገውም። እንዲሠራ መፍቀድ ብቻ ነበረበት።

መጽሐፍ ቅዱስ ለዚህ አንድ ቃል አለው፦ ማመን። ቃሉ አርጅቷል። ብዙዎች በውስጡ የሚሰሙት ሊረጋገጥ የማይችልን ነገር እውነት ነው ብሎ መቀበልን ነው። የታሰበው ግን ሌላ ነው። ማመን ማለት፦ በእርሱ መታመን ማለት ነው። ሊረዳ ለሚችል ራስን አሳልፎ መስጠት። ሁሉን መረዳት አያስፈልግዎትም። ይህን ብቻና በመጀመሪያ ይህን፦ ይቅር የሚለው፣ የሚፈውሰውና የሚያድነው እርሱ ነው። ወደ እርስዎ እንዲቀርብ መፍቀድ አለብዎት። ለእርሱ መከፈትና እንዲገባ መፍቀድ።

ከዚያስ ምን ይሆናል? አንድ ዓረፍተ ነገር እንዲህ ይናገረዋል፦

እንግዲህ በእምነት ጻድቃን ስለ ተባልን ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም አለን።[28]

---

28. ሮሜ 5፥1

ጻድቃን ተባልን – ይህ ነጻ መለቀቅ ነው። ሰላምም። እያንዳንዱ ሌላው እንደገና ይጀምር እንደ ሆነ የሚጠብቅበት የተኩሰ አቁም ሰምምነት አይደለም። ሰላም። ጉዳዩ ተጠናቋል። እኔ ሰላጠናቀቅሁት አይደለም። እርሱ በገዛ አካሉ በእንጨት ላይ ሰለ ተሸከመው ነው እንጂ።

ሦስት ነገሮች የዚህ አካል ናቸው። ይህ ግፊት አይደለም። ግብዣ ነው።

መመለስ። ይህ መጀመሪያ መልካም መሆን፣ ከዚያም መምጣት ማለት አይደለም። አቅጣጫ መቀየር ማለት ነው። ራስን ለመፈወስ መሞከርን ማቆም። እንደማይቻል መቀበል። መመለስ በድሮ ቃል ንሰሐ የሚባለው ነው።

መጠመቅ። ጥምቀት በአካል ሁሉ የሚፈጸም ምልክት ነው። ሰው በውኃ ይጠልቃል፤ እንደገናም ይወጣል። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦ ከእርሱ ጋር ተቀበርን።[29] ያን ጊዜ የነበርሁት ሰው በደሉ ወደ ቀረበት ሰፍራ ይቀመጣል። የሚወጣውም ሕያው ለሆነው ለእርሱ ነው። በጥምቀት ሰው ለአዲስ ጌታ፣ ለንጉሡ ለኢየሱስ መሆኑን ይመስክራል።

የአንድ ኅብረት አካል መሆን። ይህን መንገድ ብቻውን የሚሄድ ማንም የለም። የኢየሱስ የሆነ ከብዙ ሌሎች ጋር የአንድ ኅብረት አካል ነው። ሌሎቹ ያስፈልጉዎታል። ሌሎቹም እርስዎን ያስፈልጓቸዋል።

አሁንም መጨረሻው። መጨረሻ አይደለም፤ መጀመሪያ ነው። ሁሉም የጀመረበት ዓረፍተ ነገር፦ ሰለ እኛ ሞተ የሚል ነበር። አሁን ክርስቲያኖች በዚህ ምን ማለታቸው እንደ ሆነ ያውቃሉ። በደላችን የእርሱ ሰላልነበረ ወደ ራሱ ወሰደው። በገዛ አካሉ ወደ ሞቱ ተሸክሞ ወሰደው። ከእርሱ ጋር ወደ ውስጥ ወሰደን፤ ከእርሱም ጋር ወደ ውጭ አወጣን። ሕያውም ነው።

ከእንግዲህ ሊያሰተካክሏቸው የማይችሏቸው ነገሮች አሉ። ይህ እውነት ሆኖ ይቀራል። ነገር ግን የተሸከማቸው አንድ አለ። ይህ የምሥራቹ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ወንጌል ብሎ ይጠራዋል። እኔ አምናለሁ፦ እውነት ነው። ለእርሰዎም ነው።

29. ሮሜ 6፥4



አንድ ሰው ከሁለት ሺህ ዓመት በፊት ተገደለ። ወዳጆቹ በኋላ እንዲህ አሉ፦ ይህ ስለ እኛ ነበር።

ይህ ምን ማለት ነው? አንድ ሰው ስለ ሌሎች ሊሞት ይችላል? ይህስ ከእኔ ጋር ምን ግንኙነት አለው?

ይህ መጽሐፍ ጥያቄውን እስከ መጨረሻው ይመረምራል። በእኛ ላይ ያለውን ችግር፣ እግዚአብሔር በእውነት ምን ዓይነት እንደ ሆነና አንድ ሞት አንድን ነገር ለምን ሊለውጥ እንደሚችል ይናገራል።

መስቀሉ ከምልክት በላይ ነው። ወደ ዘላለም ሕይወት የሚያስገባ መውጫ ነው።

በእውነት ማወቅ ለሚፈልጉ ሁሉ።